# ወርሃዊ የአየር ጠባይ
# ግምገማና እና ትንበያ መጽሔት

## ከኦክቶበር 1-31/2021 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ እንዲሁም

## ከኖቬምበር 1-30/2021 የሚኖረው የአየር ጠባይ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ኖቬምበር 2021
አዲስ አበባ

**ርዕስ** **ገፅ**


እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 31/2021 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ ... 3
ካርታ 6 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 31/2021 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ... 4
ካርታ 7 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 31/2021 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት ... 5
ካርታ 8 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 31/2021 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር ... 6
እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 31/2021 የነበረው የአየር ጠባይ በእርሻ ... 7
ሥራ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ... 7
ካርታ 9 ከኦክቶበር 1 እስከ 31/2021 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ... 7
እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 31/2021 የነበረው የአየር ጠባይ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ... 8
ካርታ 10 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 31/2021 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ... 8
እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 30/2021 የሚኖረው የአየር ... 9
ጠባይ አዝማሚያ ... 9
እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 30/2021 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ... 9
እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 30/2021 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በውሀው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ... 10


## እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 31/2021 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ

ባለፈዉ የኦክቶበር ወር አብዛኛዉን ጊዜ ደረቅ፣ ፀሃያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ በአብዛኛዉ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ አመዝኖባቸዉ ተስተዉሏል፡፡ ይሁን እንጂ በመጀመሪያዎቹ አስር ቀናትና በመጨረሻዎቹ ጥቂት ቀናት ላይ ዕርጥበታማዉ የአየር ሁኔታ በመጠናከሩ በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የተሻለ የደመና ሽፋን ተስተዉሏል፡፡ በመሆኑም በአብዛኛዉ አማራ፣ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ በምዕራብ፣ መካለኛዉና ደቡብ ኦሮሚያ፣ በጋምቤላ፣ በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች፣ በሲዳማ እና አፋር ክልል ደቡባዊ ክፍሎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ ዝናብ የተመዘገበ ሲሆን፤ ከነበረዉ ጠንካራ የደመና ክምችት በወሩ የመጀመሪያዎቹ አስር ቀናት ላይ አልፎ አልፎ ባሉት ቀናት ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ለጥቀስም በመተሓራ 36.0፣ በጊዳ አያና 36.0፣ በቦሬ 34.7፣ በኢጃጂ 70.6፣ በካቺስ 38.4፣ በሻምቡ 30.2፣ በጊኒር 42.0፣ በጃራ 37.8፣ በበደሌ 57.8፣ በቡሌ ሆራ 38.4፣ በቴፒ 36.8፣ በቡኢ 47.0፣ በደባርቅ 39.4 እና በደብረወርቅ 39.7 በሚሜ ይገኙበታል፡፡


ባለፈዉ የኦክቶበር ወር የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከቦታ ሽፋን አንጻር ሲገመገም በሁሉም የወለጋ ዞኖች፣ በኢሉባቦርና ጅማ፣, በጉጂና ቦረና፣ በአርሲና ምዕራብ አርሲ፣ በምዕራብና ምስራቅ ሐረርጌ፣ በሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ በሰሜን ወሎ፣ በሰሜንና ደቡብ ጎንደር፣ በሁሉም የቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ የጋምቤላ፣ የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል እና የሲዳማ ክልል ዞኖች ላይ ከ25-263 ሚሜ የሚደርስ ከ5-19 ቀናት ያህል ዝናብ የነበራቸዉ ሲሆን፤ በአፋር ክልል ዞኖች፤ ከሱማሌ ክልል በደገሃቡር፣ በሊበንና አፍዴር ዞኖች ላይ ከ5-25 ሚሜ የሚደርስ ከ02 ላነሱ ቀናት ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 6 እና 7)፡፡

ባለፈዉ የኦክቶበር ወር የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር በቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ በጋምቤላ፣ በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች እንዲሁም በሲዳማ ክልል ሁሉም ዞኖች፣ በወለጋና ሸዋ ከሞላ ጎደል በሁሉም ዞኖች ላይ፣ በአርሲና ምዕራብ አርሲ፣ በአብዛኛዎቹ የባሌ ዞን፣ በምዕራብና ምስራቅ ሐረርጌ፣ በሲቲ፣ በፋፈንና ደገሃቡር፣ በሰሜን ጎንደር፣ በምስራቅና ምዕራብ ጎጃም፣ በጥቂት የደቡብ ወሎና ሰሜን ሸዋ (03)፣ ከአፋር ክልል ዞን 01፣ 05ና 03 ላይ መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ ተመዝግቧል (ካርታ 8) ፡፡


ካርታ 6 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 31/2021 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ካርታ 7 ኢ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 31/2021 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት



ካርታ 8 ኢ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 31/2021 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር





መደበኛ በታች  መደበኛ  ከመደበኛ በላይ

# እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 31/2021 የነበረው የአየር ጠባይ በእርሻ ሥራ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው የኦክቶበር ወር ከመጀመሪያዎቹ አስር ቀናት በስተቀር የተቀሩት ቀናት ደረቃማ የእርጥበት ሁኔታ (dry moisture condition) በአብዛኞዎቹ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ  አመዝኖ እንደነበረ ከተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሰበሰቡ የግብርና ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ ይህም ሁኔታ በመድረቅ ሂደት ውስጥ ለሚገኙ ሰብሎች  አዎንታዊ ሚና የነበረው ቢሆንም በሌላ መልኩ በተለለያየ ምክንያት ዘግይተው ለተዘሩና እድገታቸውን ላላጠናቀቁ እንዲሁም ተጨማሪ እርጥበት ለሚያስፈልጋቸው የመኸር ጊዜ ሰብሎችም ሆነ ለቋሚ ተክሎች አሉታዊ ጎን የነበረው ሲሆን በተጨማሪም በግጦሽ ሳር እና በመጠጥ ውኋ አቅርቦት ላይ አሉታዊ ጎን ነበረው። ሆኖም ግን በመጀመሪያዎቹ የወሩ አስር ቀናት አጋማሽ በኋል ለእርጥበት መጨመር ምቹ ከነበረው የሚቲዎሮሎጂ ክስተት መጠናከር ጋር ተያይዞ በብዙ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ከመጠነኛ እስከ ከፍትኛ የሚደርስ የእርጥበት ይዘት እንደነበራቸው የተተነተኑ መረጃዎች ያመለክታሉ። ይህም ተጠናክሮ የታየው እርጥበታማ ሁኔታ እድገታቸውን ላልጨረሱና በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የመኸር ሰብሎችም ሆነ ለቋሚ ተክሎች እድገት የሚያስፈልጋቸውን እርጥበት ከማስገኘት አንጻር አዎንታዊ ሚና ነበርው። በተጨማሪም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው ለሆኑት የአርብቶ አደርና የከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎቾ የተለያዩ የግብርና እንቅስቃሴዎችን እንዲያከናውኑ  አዎንታዊ ሚና የነበረው ሲሆን ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሻሻልም ገንቢ ሚና ነበረው። ሆኖም ግን አስቀድመው ተዘርተው እድገታቸውን ለጨረሱ እና በመድረቅ ሂደት ውስጥ ለሚገኙ አንዳንድ የመኸር ወቅት ሰብሎች የነበረው እርጥበታም ሁኔታ አሉታዊ ጎነ ነበረው። በተጨማሪም ከእርጥበት መጨመር ጋር ተያይዞ ለሚፈጠሩ እንደዋግ ያሉ የሰብል በሽታዎች በአንዳንድ አካባቦዎቾ ላይ እንዲከሰቱ አስተቃጽዖ ነበረው (ካርታ 9)፡፡


ካርታ 9    ከኦክቶበር 1 እስከ 31/2021 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



# እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 31/2021 የነበረው የአየር ጠባይ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

እ.ኤ.አ 1-31 ኦክቶበር 2021 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረውን ተፅዕኖ በተመለከተ የተሻለ የእርጥበት መጠን በምዕራብ፣ በደቡብ ምዕራብ፣ በደቡብ ምስራቅና በደቡባዊ የሀገሪቱ አጋማሽ ተፋሰሶች ላይ ተስተውሏል፡፡ በዚህ መሰረት ከፍተኛ እርጥበት የነበራቸው ተፋሰሶች በአብዛኛው ኦሞ ጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ ባሮ አኮቦ፣ የላይኛው እና የመካከለኛው አባይ፣ የላይኛው ዋቤ ሸበሌ እና የታችኛው ተከዜ፣ ተፋሰሶች ናቸው፡፡ በተጨማሪም የላይኛው እና የመካከለኛው አዋሽ፣ የመካከለኛው ዋቢሸበሌ፣ በጥቂት የላይኛው ስምጥሸለቆና ኦሞጊቤ እናንዲሁም የመካከለናው ተከዜ የታችኛው ክፍል ተፋሰሶች ደግሞ መጠነኛ እርጥበት የተሰተዋለባቸው ናቸው (ካርታ 10) ፡፡

ካርታ 10 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 31/2021 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



## እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 30/2021 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ

በሚቀጥለው ወር በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ጠባይ በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ እንደሚያመዝን የሚጠበቅ ሲሆን፤ በአንዳንድ ደጋማ የሀገሪቱ ቦታዎች ላይ የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ በተለይም ከወሩ አጋማሽ በኋላ ሊጠናከር እንደሚችል ይጠበቃል፡፡ በሌላ በኩል አልፎ አልፎ ከሚኖረዉ የደመና ሽፋን ጋር ተያይዞ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ በተዳከመ ሁኔታ እስከ ወሩ አጋማሽ ድረስ በደቡብ ምዕራብና በደቡብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ እንደሚኖር ይጠበቃል።

በዚህም መሰረት <u>ከኦሮሚያ ክልል ምዕራብና ምሥራቅ ወለጋ፣ ኢሉአባቦራ እንዲሁም የጉጂ፣ የቦረና፣ የአረሲ እና ባሌ ዞኖች፤ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል የአሶሳና የከማሺ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል የደቡብ ጎንደር፣ የምዕራብ ጎጃም፤ ከደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ደግሞ የከፋና የቤንች ማጂ፣ የደቡብ ኦሞ እና የሰገን ሕዝቦች፣ የጌዲዮ፣ የጋሞ እና የጎፋ ዞኖች እንዲሁም በሶማሌ ክልል የሚገኙት የአፍዴር እና የሊበን ዞኖች በተለያዩ ሥፍራዎቻቸው ላይ በአብዛኛው ከመደበኛው ጋር የተቀራረበ ዝናብ የሚጠበቅባቸው ሲሆን፤ የተቀሩት የሀገሪቱ ሥፍራዎች ደረቅ የአየር ሁኔታ አመዝኖባቸው ይቆያሉ፡፡</u>

## እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 30/2021 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በመደበኛ ሁኔታ የኖቬምበር ወር በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቃማ የእርጥበት ሁኔታ የሚያመዝን ሲሆን፤ በአብዛኛው የመኸር ሰብሎች ስብሰባና የድህረ ሰብል ስብሰባ የሚከናወንበት ወቅት ነው፡፡ በአንፃሩ የደቡብና ደቡብ አጋማሽ የሀገሪቱ አካባቢዎች መጠነኛ የሆነ እርጥበት የሚያገኙበት ወር ነው፡፡

በተሰጠው የአየር ሁኔታ ትንበያ መሠረት በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች የበጋው ደረቃማ የእርጥበት ሁኔታ እንደሚያመዝን ይጠበቃል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በአንዳንድ ደጋማ አካባቢዎች ላይ የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ እንደሚጠናከርና የውርጭ ክስተት ሊኖር እንደሚችል በትንበያው ተመልክቷል፡፡ ይህም ደረቅ ሁኔታ የእድገት ጊዜያቸውን እየጨረሱ ላሉና ተጨማሪ የውሃ አቅረቦት ለማይፍልጉ ሰብሎች እንዲሁም የእድገት ጊዜያቸውን ጨርሰው ለመሰብሰብ ዝግጁ

የሆኑ ሰብሎችን ለመሰብሰብ ምቹ ሁኔታን የሚፈጥር ሲሆን፣ ከደረቃማው ሁኔታ ጋር ተያይዞ የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ ጠንካራ ሊሆንና የውርጭ ክስተትንም በአንዳንድ አካባቢዎች ሊያስከትል ስለሚችል ይህም ሁኔታ በተለይም በአንዳንድ አካባቢዎች በአበባና ፍሬ በመሙላት ላይ ያሉ ሰብሎችን ሊጎዳ ስለሚችል አርሶ አደሮች አስፈላጊውን ጥንቃቄ ለማድረግ እንዲችሉ የግብርና ባለሙያዎች ቅርብ ክትትልና አስፈላጊውን እገዛ እንዲያደርጉ ከወዲሁ ይመከራል፡፡ በአንፃሩ ከሚጠናከሩ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ጋር ተያይዞ በተለይም በደቡብ ምዕራብና በደቡብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው እርጥበታ እንደሚኖር ይጠበቃል ፡፡ ይህም የሚጠበቀው እርጥበት በተለያየ እድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎች እንዲሁም በመጠን አነስተኛ ቢሆንም በደቡብና በደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውሀ አቅርቦት በተወሰነ መልኩ በጎ ሚና ይኖረዋል፡፡

## እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 30/2021 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በውሀው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥለው ኖቨምበር ወር በአብዛኛው የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ የበጋው ደረቅና ፀሃያማ ሁኔታ የሚያመዝን ሲሆን፤ በሌላ በኩልም አልፎ አልፎ ከሚኖረዉ የደመና ሽፋን ጋር ተያይዞ ከመጠነኛ እስከ እርጥበታማ የእርጥበት መጠን በተዳከመ ሁኔታ እስከ ወሩ አጋማሽ ድረስ በደቡብ ምዕራብና በደቡብ አጋማሽ የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ እንደሚኖር ይጠበቃል። ይህንን ተከትሎ በአብዛኛው ባሮአኮቦ፣ ገናሌዳዋ፣ የመካከለኛውና የታችኛው ኦሞጊቤ፣ የአባይ የላይኛውና የታችኛው አጋማሽ፣ የላይኛው ዋቢሸበሌ፣ የታችኛው ስምጥሸለቆ እና ኦጋዴን ተፋሰሶች ላይ በአብዛኛው በተለያዩ ቦታዎቻቸው ላይ መጠነኛ የእርጥበት መጠን እንደሚያገኙ ትንበያው ይጠቁማል። በሌላ በኩል የተቀሩት የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ ደረቅ የአየር ሁኔታ አመዝኖባቸው ይቆያሉ፡፡